የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ
የፌዴሬሽን ምክር ቤት

The House of Federation
of
the Federal Democratic Republic
of Ethiopia

ቁጥር
No. አመሠሃ/ፈ፲፫/13278

ቀን
Date 03/11/2018

ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
አዲስ አበባ
ለአቶ ወርቅነህ ሁነኛው
ባሉበት

ጉዳዩ፡- የምክር ቤቱን ውሳኔ ስለማሳወቅ፣

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 62(1) እና 83(1) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሕገ መንግስታዊ ክርክር ሲነሳ ሕገ መንግስቱን በመተርጎም ውሳኔ ይሰጣል፡፡

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር በመዘርዘር በወጣው አዋጅ ቁጥር 1261/2013 አንቀጽ 22(1) እና አንቀጽ 80 መሰረት ምክር ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና አስገዳጅ መሆኑን እንዲሁም ማንኛውም ሰው፣ የፌዴራልና የክልል ፍርድ ቤቶች፣ የፌደራልና የክልል መንግስታት የመንግስት፣ ባለሥልጣናት እና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት የምክር ቤቱን ውሳኔ የማክበር፣ የማስፈፀም እና የመፈጸም ግዴታ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሰኔ 29 ቀን 2018 ዓ.ም 6ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 5ኛ ዓመት 2ኛ መደበኛ ጉባዔው አቶ ወርቅነህ ሁነኛው ባቀረቡት የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ላይ ከሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መርምሮ የሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ 10 ገጽ ከዚህ መሸኛ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ የተላከላችሁ ስለሆነ በምክር ቤቱ ውሳኔ መሠረት እንዲፈፀም አስታውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

አገኘሁ ተሻገር ገሠሠ
የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ

ግልባጭ
- ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ
  አዲስ አበባ

በፌዴሬሽን ምክር ቤት
- ለሕገ መንግስት ትርጉም የውሳኔ አፈፃፀም ክትትል ቋሚ ኮሚቴ

በፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽ/ቤት
- ለሕገ መንግስት ትርጉምና የሕጎች ሕገ መንግስታዊነት ክትትል ዳይሬክቶሬት

ስልክ. 011-1-223322 Tell. 011-1-242303
ፋክስ 011-1-242304 Fax 011-1-242309
E-mail: hofethiopia@gmail.com
Web Site: https//: www.hofethipia gov.et
ፖ.ሣ.ቁ 20212/1000 P.o.Box
አዲስ አበባ Addis Ababa

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 6ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 5ኛ ዓመት የሥራ ጊዜ፣ 2ኛ መደበኛ ጉባዔ ሰኔ 29 ቀን 2018 ዓ.ም

መ/ቁ 151

አመልካች፡- አቶ ወርቅነህ ሁነኛው

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ጠቅላይ ዓ/ሕግ

ምክር ቤቱ አጣሪ ጉባኤው የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መርምሮ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

ጉዳዩ ለሕገ መንግሥት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 221848 በቀን 4/8/2014 ዓ.ም የሠጠው ውሳኔ ሕገመንግሥታዊ መብቴን ይጥሳል በማለት የሕገመንግስት ትርጉም እንዲሰጥለት በቀን6/10/2014 ዓ.ም ለጉባኤው ፅፎ ባቀረበው አቤቱታ መነሻነት ሲሆን የወንጀል ጉዳይን የተመለከተ ነው፡፡

ተጠሪ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ በመሰረተው ክስ ተከሳሽ የጦር መሣሪያ ለመቆጣጠር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀፅ 4(1) እና 22(3) ሥር የተመለከተውን የሕግ ድንጋጌ በመተላለፍ በቀን 1/13/2013 ዓ.ም ከቀኑ በግምት 5፡00 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ በቢሾፍቱ ከተማ ቁርቁራና ደንቢ በተባለ ቀበሌ ውስጥ 1ኛ ትልቁ የቱርክ ሽጉጥ ቁጥሩ ፎዞ181014401 የጥይቱ ብዛት 7 የሆነ 2ኛ ትንሹዋ የቱርክ ሽጉጥ ቁጥሩ 8 እያ41417385 የሆነ የጥይት ብዛት 4 ከሆነው ጋር በንግድ ቤቱ ውስጥ ከሕግ አግባብ ውጪ ደብቆ በፖሊስ ፍተሻ ሲደረግ ስለተገኘበት ብዛት ያለውን የጦር መሳሪያ ከፍቃድ ውጭ በህገ ወጥ መንገድ በመያዝ ወንጀል ተክሷል የሚል ነው፡፡

አመልካችም በችሎት ቀርቦ ማንነቱ ተረጋግጦ ክሱ ከተነበበለትና እንዲረዳው ከተደረገ በኃላ ድርጊቱን ስለመፈፀሙ ተጠይቆ አልፈፀምኩም የጦር መሳሪያውን በንግድ ቤቴ ውስጥ እንዴት እንደተቀመጠ እና ማን እንዳስቀመጠው አላውቅም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቷል፡፡

በዚህም መሰረት ተጠሪ 2 የሰው ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ የቀረቡት ምስክሮች የፖሊስ አባላት ሲሆኑ ለቀረበው ክስ ማስረጃ ሊሆኑ የቻሉበት ዋነኛ ምክንያት የአመልካች ባለቤት ባቀረበችው አቤቱታ መነሻነት በተደረገው ብርበራ ላይ ተሳታፊ በመሆናቸው ነው፡፡ የሰጡት የምስክርነት ቃልም የአመልካች ባለቤት የጦር መሳሪያው ያለበትን ቦታ ከጠቆመችን በኃላ ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ሁለት የጦር መሳሪያዎች ካዝናው ሲከፈት ከካዝናው ውስጥ መያዛቸውንና እነዚሁ መሳሪያዎች ሕጋዊ ፍቃድ እንዳልነበራቸው ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ በማለፅ አስረድተዋል፡፡ በተጨማሪም 1 ገፅ የሰነድ ማስረጃ ቀርቦ እንዲሰማ ተደርጓል፡፡

ፍ/ቤቱም ተጠሪ ያቀረበውን ክስ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ እንደ ክሱ ያስረዳ በመሆኑ አመልካች የቀረበበትን ክስ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 142 (1) መሰረት ይከላከል ተብሏል፤ አመልካችም 3 የመከላከያ ምስክሮቹን አቅርቦ አሰምቷል፡፡

አመልካች ባቀረባቸው የመከላከያ ምስክሮች 1ኛ የመከላከያ ምስክር በሞባይል መሸጫው ውስጥ አንደሚሰሩ ጠቅሰው በሰጡት ቃል ለምርመራ መነሻ የሆነውን መረጃ ለሕግ አስከባሪ አካላት አቤቱታ ያቀረበችው እና መሳርያወቹ ያለበትን ቦታ ለይታ ለፖሊስ የመራችው ሊዲያ ቱሉ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ * የፌዴሬሽን ምክር ቤት *

የተባለች የአመልካች ባለቤት እንደሆነች አመልካች መጣሪያው ተገኝ የተባለበት የንግድ መደብር ሱቅ እነደማይመጣ ይህንንም ሱቅ በበላይነት የምታስተዳድረው ባለቤቱ እንደሆነች መሳሪያ ተገኝ የተባለበት የካዝና ቁልፍ እርሷ ጋር እንደሚገኝ ይህንንም ካዝና ማታ ማታ ሱቁ ሲዘጋ ሞባይል እንደምታሳድርበትና ጠዋት ጠዋት ከዚሁ ካዝና ውስጥ ሞባይሎችን እንደምታወጣ መስክረዋል፡፡ 2ኛ እና 3ኛ የመከላከያ ምስክሮች በአመልካች እና ባለቤቱ ሊዲያ ቱሉ መሐከል አለመግባባት መኖሩን በተዳጋጋሚ ለማስታረቅ ሙከራ ማድረጋቸውን፣ በዚህም በቢሾፍቱ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 18370 የፍች እና ተያያዥ ክርክሮች እንዳላቸው አስረድተዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የተጠሪ ምስክሮችን እና የአመልካች መከላከያ ምስክሮችን መስማት በዚሁ ከተጠናቀቀ በኃላ አመልካች በተከሰሰበት የሕግ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ መሆን አለመሆኑን መርምሯል፡፡ በዚህም ፍርድ ቤቱ አመልካች የጦር መሳሪያው በንግድ ሱቁ አለመገኘቱን ወይም መሳሪያው በንግድ ሱቁ የተቀመጠው በሌላ ሰው አማካኝነት ስለመሆኑ አላስረዳም፡፡ ስለሆነም አመልካች ያቀረባቸው የመክከላከያ ምስክሮች አቃቤ ህግ ካቀረባቸው ምስክሮች በተሻለ ሊያሳምን በሚችል ሁኔታ ያላረጋገጠ በመሆኑ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ግራ ቀኙ የቅጣት አሰተያየታቸውን እንዲያቀርቡ ተደርጎ አመልካች የአምስት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እሰራት እና የ3000 (ሶስት ሺህ) ብር የገንዘብ መቀጮ ለመንግሥት ገቢ እንዲያደርጉ ተብሎዋል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቀር የተሰኙ በመሆኑ የይግባኝ ቅሬታቸውን እና የሰበር አቤቱታቸውን በየደረጃው ለሚገኙ ፍ/ቤቶች ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙም ሆነ አቤቱታው ተቀባይነት ሳያገኝ የሰር ፍ/ቤት ውሳኔ በትዕዛዝ ፀንቷል፡፡

አመልካችም ለጉባኤው ባቀረበው አቤቱታ የጦር መሳሪያው ተገኘ በተባለበት እለት በስፍራው አልነበርኩም፣ የሱቁም ቁልፍ በባለቤቴ እጅ የሚገኝ እንጂ አመልካች ከፍቼ የማልዘጋው አንደሆነ የቀረቡት የመከላከያ ምስክሮች ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ ስለሆነም ጥፋተኛ ተብዬ የእስራት እና የገንዘብ ቅጣት ውሳኔ የተላለፈብኝ እኔ ባልፈጸምኩት ጥፋት በመሆኑ የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 20 የተረጋገጠልኝን ነፃ ሆኖ የመገመት እና የነፃነት መብቴን የሚጥስ በመሆኑ የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጥልኝ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

ጉባኤውም ጉዳዩን ከመረመረ በኃላ አመልካች ባቀረቡት የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ላይ 1ኛ የተከሰሰ ሰው ነፃ ሆኖ የመገመት መብት በዓ/ሕግ ላይ የሚጥለው የማስረዳት ሸክም በሕገ መንግስቱ ተቀባይነት ያለው አነስተኛ መመዘኛ ምንድን ነው ? 2ኛ የፍ/ቤቶች የጥፋተኝነት ፍርድ በተራ ቁጥር 1 ከተመለከተው የዓ/ሕግ የማስረዳት ሸክም አነስተኛ መመዘኛ እና ከአመልካቹ ነፃ ሆኖ የመገመት መብት አንፃር ያለው ሕገመንግስታዊነት እንዴት ይታያል ? የሚሉ ጭብጦችን በመለየት ተጠሪ መልስ እንዲያቀቡ በጉዳዮች አቀራረብና አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2012 አንቀጽ 24 መሰረት አዛል፡፡ ተጠሪም በደብዳቤ ቁጥር 01-29441 በቀን 12/10/2015 ዓ.ም የተፃፈ. 4 ገፅ መልስ አቅርባል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘትም በህጎቻችን የምንከተለው የማስረጃ ማረጋገጥ ምዘና (standadrd of proof) በግልፅ ባይገለፅም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 42(1) (ሀ) መሰረት ዓ/ሕግ ክስ ለመመስረት ተጠርጣሪው ላይ በቂ ማስረጃ ሲያገኝ ብቻ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 141 መሰረት ፍ/ቤቱ ተከሳሹ ላይ በቂ ማስረጃ ካልቀረበ ወይም በዓ/ህግ የቀረበው ማስረጃ በቂ ሆኖ ሳያገኘው የቀረ እንደሆነ ተከሳሹ በነጻ እንደሚለቀቅ ተደንግጓል፡፡ ከነዚህ ከሁለቱ ድንጋጌዎች

የምንረዳው ተቀባይነት ያለው የዓ/ሕግ አነስተኛ የማስረዳት ሸክም ያቀረበውን ክስ በበቂ ማስረጃ ማረጋገጥ ነው፡፡

ከአመልካቹ ነፃ ሆኖ ከመገመት መብት ጋር በተያያዘ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 20(3) ሥር የተከሰሱ ሰዎች መብት ሲደነግግ በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ በተከሰሱበት ወንጀል እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር፤ በምስክርነት እንዲቀርቡ ያለመገደድ መብት አላቸው በማለት ይደነግጋል፡፡ ይህም ሲባል ፍ/ቤቱ በግራ ቀኙ መካከል የቀረበውን ማስረጃ መዝኖ ጥፋተኛ ነው እስከሚል ድረስ እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት እንዳለው የሚያስገነዝብ ነው፡፡

አሁን በተያዘው ጉዳይ አመልካች የተከሰሰበት የወንጀል ክስ አስመልክቶ ዓ/ሕግ የሰው ምስክሮችንና የሰነድ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ አመልካችም የራሱን መከላከያ ምስክሮች አቅርቦ ራሱን እንዲከላከል መብቱ የተጠበቀና መከላከያ ምስክሮቹ ቀርበው ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙ ምስክሮች ከተሰሙ በኃላ ሂደቱን ጠብቆ መዝገቡን መርምሮ አመልካች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ስለሰጠ የአመልካች ነፃ ሆኖ የመገመት መብት ስላልተጣሰ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ውድቅ እንዲደረግ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ጉባኤው አመልካች ካቀረቡት የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ እና በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የአመልካችን ንፁህ ሆኖ የመገመት ሕገ መንግስታዊ መብትን ይጥሳል በማለት እምነት ያሳደረበት ነጥብ እና የዐቃቢ ሕግ (የተጠሪን) መልስ መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ ሰፊ ጥናትና ምርምር ካደረጉ ባለሙያዎች እና በዘርፉ እየሰሩ ካሉት ተቋማት ተጨማሪ ሙያዊ አስተያየቶች እንዲቀርብ ጥሪ አቅርቧል፡፡ ሃሳብ እንዲሰጥባቸው በጉባኤው የተለዩት መነሻ ጭብጦች በሁለት ነጥቦች ላይ የሚያጠነጥኑ ሲሆኑ እነሱም፡- የተከሰሰ ሰው ነፃ ሆኖ የመገመት ሕገ መንግስታዊ መብት በዓ/ሕግ ላይ የሚጥለው የማስረዳት ሸክም በሕገ መንግስቱ ተቀባይነት ያለው አነስተኛ መመዘኛ ምንድን ነው? እና የፍ/ቤቶቹ የጥፋተኝነት ፍርድ በተራ ቁጥር 1 ላይ ከተመለከተው የዓ/ሕግ የማስረዳት ሸክም አነስተኛ መመዘኛ እና ከአመልካቹ ነፃ ሆኖ የመገመት መብት አንፃር ያለው ሕገመንግስታዊነት እንዴት ይታያል ?

በዚህም ጉባኤው ያቀረበውን ጥሪ መሠረት በማድረግ ከአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ፤ ከሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ፤ ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ቢሮ አና ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፍትሕ ቢሮ የሙያ አስተያየት ቀርቧል፡፡ ከዩንቨርሲቲዎቹ አና ከፍትሕ አካላቱ የቀረቡት አስተያየቶች ይዘት በአጠቃላይ ሲታይ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ የአመልካችን ሕገ መንግስታዊ ነጻ ሆኖ የመገመት መብት የጣሰ ነው በማለት የቀረቡ ናቸው፡፡

ከአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ እና ከሲቪል ሰርቪስ ዩንቨርሲቲ የቀረቡ አስተያየቶች ይዘት በዋናነት የፍርድ ቤቱ ውሳኔ የአመልካችን በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠለትን ነጻ ሆኖ የመገመት መብት የሚጥስ መሆን አለመሆኑ ላይ መሠረት ያደረጉ ናቸው፡፡ በዚህም ነጻ ሆኖ የመገመት መብት የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 14 አንጻር ትንታኔ አቅርበዋል፡፡ በተለይ የስምምነቱን አፈጻጸም የመከታተል ስልጣን የተሰጠው የሰብአዊ መብቶች ኮሚቴ በመጀመሪያ በማብራሪያ ቁጥር 13 ቀጥሎም በማብራሪያ ቁጥር 30 ነጻ ሆኖ የመገመት መብትን አስመልክቶ የሰጠው ትርጉም እንደ መነሻ ተወስዷል፡፡ በዚህ ማብራሪያ 30ኛው ፓራግራፍ መሰረት ማንኛውም ተከሳሽ ነጻ ሆኖ የመቆጠር መብት አለው የሚባለው ዓቃቤ ሕግ እንደ ክሱ አቀራረብ ክሱን በማስረጃ ሳያስረዳ ሲቀር፣ ማንኛውም አጠራጣሪ ነገር ተከሳሹን በሚጠቅም መልኩ መተርጎም ያለበት መሆኑ እና ተከሳሹ ነጻ ሆኖ የመገመት መብቱ ቀሪ የሚሆነው አቃቤ ህጉ ከምክንያታዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ * ጠቅላይ ፍ/ቤት * የፌዴሬሽን ምክር ቤት

ጥርጣሬ ውጪ ክሱን ሲያረጋግጥ እንደሆነ ማብራሪያ ተሰጥቶበታል፡፡ አሁን በተያዘው ጉዳይ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ህጉ የአቃቤ ህግን የማስረዳት ደረጃ በግልጽ ያልደነገገ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች የተለያየ መመዘኛ እንደሚጠቀሙ እና በአመልካች ላይ ተፈጻሚ ያደረጉት በቂ ማስረጃ በመቅረብ የማስረዳት ደረጃ በሕገ መንግስቱ ከተረጋገጠው ነጻ ሆኖ የመገመት መብት ጋር የሚቃረን መሆኑን ደምድመዋል፡፡

ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ቢሮ እና ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፍትሕ ቢሮ በበኩላቸው ባቀረቡት አስተያየት በወንጀል ሥነ ሥርዓት ህጉ ቁጥር 141 መሠረት አቃቤ ህግ ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማድረግ በቂ ማስረጃ ካላቀረበ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹን በነጻ እንደሚለቀው ተደንግጓል፡፡ በዚህ መሠረት የአቃቤ ህግ ግዴታ በቂ ማስረጃ ማቅረብ ነው፤ ዐቃቤ ህግ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በጸዳ አግባብ የማስረዳት ግዴታ የለበትም የሚል ሃሳብ አቅርበዋል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አሁን በቀረበው ጉዳይ አቃቢ ህጉ አመልካችን ጥፋተኛ ለማስባል በቂ ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ አመልካችን ጥፋተኛ በማለት እንዲቀጣ መወሰኑ የአመልካችን የግል ነጻነት መብት ይጥሳል የሚል አስተያየት አቅርበዋል፡፡

በጉባኤው ጥሪ አማካኝነት ከባለሙያዎች እና ተቋማት የቀረቡት አስተያየቶች እና ሃሳቦች ዝርዝር ማብራርያ ከዋናው መዝገብ ጋር ተያይዞ የሚገኝ ሲሆን ጉባኤው በጉዳዩ ላይ የሰጠው የውሳኔ ሃሳብ ቀጥሎ ባለው መልኩ ቀርቧል፡፡

አመልካች ያቀረበው የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ጉባኤው ለውሳኔ ሃሳብ አሰጣጥ አእንዲያመች እና በጉዳዩ ላይ በቂ መረጃ ለማግኘት ሲባል ከተጠሪ እንዲሁም በርእሰ ጉዳዩ ላይ በቂ የስራ ልምድ ካላቸው እና ምርምር ካደረጉ ተቋማት እና ምሁራን የሙያ አስተያየት በማሰባሰብ ወቅት የተገኙ ጠቃሚ መረጃዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት መዝገቡን መርምሮታል፡፡ በዚህም ለውሳኔ ሃሳብ አሰጣጥ እንዲያመች ጉባኤው ከዚህ በፊት የሙያ አስተያየት በማሰባሰብ ሂደት የቀረጸውን ጭብጥ ላይ ለውጥ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ያላገኘው በመሆኑ ጉዳዩን ለመርመር ሁለት መሠረታዊ ጭብጦች የያዘ ሲሆን እነሱም፡-

1. የተከሰሰ ሰው ነፃ ሆኖ የመገመት ህገ መንግስታዊ መብት በዓቃቢ ሕግ ላይ የሚጥለው የማስዳት ሸክም በህገ መንግስቱ ተቀባይነት ያለው ከነስተኛ መመዘኛ ምንድን ነው?

2. የፍርድ ቤቶቹ የጥፋተኝነት ፍርድ በተራ ቁጥር 1 ላይ ከተመለከተው የዓቃቢ ሕግ የማስረዳት ሸክም አነስተኛ መመዘኛ እና ከአመልካቹ ነፃ ሆኖ የመገመት መብት አንፃር ያለው ሕገ መንግስታዊነት እንዴት ይታያል? የሚሉ ናቸው፡፡

ጉባኤው ከላይ የተጠቀሱት ጭብጦች እልባት ለመስጠት እንዲቻል በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት ነጻ ሆኖ የመገመት መብት ጥበቃ ማድረጉ በዐቃቢ ሕግ ላይ የሚጥለው የማስረዳት ግዴታ ደረጃ ምን እንደሆነ፤ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ ውጪ የማስረዳት ግዴታ ይዘት እና ፍርድ ቤቱ በሕገ መንግስቱ ወንጀልን ለማስረዳት ከተቀመጠው አነስተኛ መመዘኛ አኳያ አመልካችን ጥፋተኛ ሲል ውሳኔ መስጠቱ ሕገ መንግስታዊ መሆን አለመሆኑ ቀጥሎ ባለው አግባብ ተመርምራል፡፡

1. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት የተረጋገጠው ነጻ ሆኖ የመገመት መብት በዐቃቤ ሕግ ላይ የሚጥለው አነስተኛ የማስረዳት ደረጃ ምንድን ነው?

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 20(3) ስለተከሰሱ ሰዎች መብቶች የሚደነግግ ሲሆን ከእነዚህ መብቶች መካከል አንዱ ተከሳሾች በፍርድ ሂደት ባሉበት ወቅት ነጻ ሆኖ የመገመት መብት ነው፡፡

ይሁን እንጂ ይህ መብት በተግባር ምን ማለት ነው ? ማን ላይ ምን አይነት ግዴታ ይጥላል? የሚለው ጥያቄ ምላሽ ማግኘት ያለበት ነው፡፡ በስራ ላይ ያለው የሥነ ሥርዓት ሕግ ከሕግ መንግስቱ ቀደም ብሎ የወጣ ከመሆኑ አኳያ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠውን ነጻ ሆኖ የመገመት መብት ተግባራዊ በሚያደረግ እና በተጣጣመ መንገድ የተቀረጸ ስለመሆኑ መፈተሽ ያለበት ነው፡፡

ፍርድ ቤቶች በወንጀል የተጠረጠረ ሰው የጥፋተኝነት ውሳኔ ለመስጠት ተግባራዊ ከሚያደርጓቸው የሥነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መካከል አንቀጽ 141 ነው፡፡፡ በሥነ ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 141 መሠረት ዐቃቤ ሕጉ ማስረጃውን አሰምቶ ከጨረሰ በኋላ ማፍረሻ ማስረጃ ማቀረብ አስፈላጊ ሳይሆን ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርገው ሆኖ ባልተገኘ ጊዜ እና ማስረጃው በቂ ሆኖ ሳያገኘው የቀረ አንደሆነ ተከሳሹ በነጻ እንዲለቀቅ ፍርድ ቤቱ ያዛል በማለት ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን በዐቃቢ ሕግ የቀረበው ማስረጃ ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማሰኘት በቂ ሆኖ ከተገኘ ተከሳሹ ሊከላከል እንደሚገባው በአንቀጽ 142 ተደንግጓል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች ውጪ ተከሳሹ የመከላከያ ማስረጃው ካቀረበ በኋላ ጥፋተኛ መሆን አለመሆኑ ለመወሰን ፍርድ ቤቱ ተግባራዊ የሚያደርገው አነስተኛ መመዘኛ ምን አንደሆነ በግልጽ አልተደነገገም፡፡ በዚህም የተነሳ በተለያየ ጊዜ ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት ፍርድ የተለያየ አገላለፅ ይጠቀማሉ፡፡ ለምሳሌ "ተከሳሽ የተከሰሰበትን የወንጀል ተግባር ስለመፈፀሙ በማስረጃ ስለተረጋገጠበት ጥፋተኛ ነው፡፡" ዓ/ሕግ ባቀረበው ማስረጃ ተከሳሽ የተከሰሰበትን ወንጀል ስለመፈፀመ በበቂ ያስረዳ ስለሆነ (በበቂ ስለተመሰከረበት) ጥፋተኛ ነው፡፡ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በጸዳ ሁኔታ ስለተረጋገጠ" ወዘተ የሚሉ ናቸው፡፡ አሁን በያዝነው ጉዳይ ፍርድ ቤቱ አመልካችን ጥፋተኛ ለማሰኘት የተጠቀመው የማስረዳት ደረጃ ዐቃቤ ሕግ በተሻለ ሁኔታ አስረድቷል የሚል ነው፡፡ ከጥቂት አስርተ ዓመታት ቀደም ብለው ይሰጡ በነበሩ ፍርዶች ደግሞ "ተከሳሽ የተከሰሰበትን ወንጀል ስለመፈፀመ ከበቂ ጥርጣሬ ውጪ የተረጋገጠበት ስለሆነ ጥፋተኛ ነው' የሚሉ ፍርዶች ነበሩ፡፡ ይህም የሚያሳየው በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ የማስረዳት ደረጃ ግልጽ መመዘኛ በስራ ላይ ውሎ የማይታይ መሆኑን ነው፡፡

አሁን ለጉባኤው በቀረበው ጉዳይ ፍርድ ቤቱ ተፈጻሚ ያደረገው የማስረዳት ደረጃ ከላይ ከተጠቀሱት የማስረዳት ደረጃዎች ያነሰ ሆኖ አመልካች ጥፋተኛ የተባለው ያቀረባቸው የመከላከያ ምስክሮች አቃቤ ህግ ካቀረባቸው ምስክሮች በተሻለ ሊያሳምን በሚችል ሁኔታ አላረጋገጠም በሚል ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው ፍርድ ቤቱ የወንጀል ድርጊቱ ስለመፈጸሙ እና አለመፈጸሙ የማስረዳት ሸክም ከዐቃቤ ሕግ በመወሰድ በአመልካች ላይ የጣለ መሆኑን ነው፡፡ አመልካችም ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣው ዐቃቤ ሕግ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በጸዳ አግባብ በማስረዳቱ ሳይሆን አመልካች ያቀረበዉ የመከላከያ ማስረጃ ዐቃቤ ሕግ ካቀረበው ማስረጃ ያነሰ አሳማኝነት ደረጃ አለው በሚል ነው፡፡ ማስረጃው የተመዘነበት አግባብ የፍትሐ ብሔር የማስረጃ ደረጃ መሰረት በማድረግ ሲሆን ከወንጀል ጥፋተኝነት የማስረዳት አነስተኛ መመዘኛ አንጻር ሕገ መንግስታዊ ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡ በኢትዮጵያ አሁን በስራ ላይ ያለው የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ የወጣው እና ወደ ትግበራ የገባው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት ወደ ስራ ከመግባቱ በፊት ነው፡፡ ስለሆም የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕጉን ከሕገ መንግስቱ በተጣጣመ መንገድ መተግበር የሁሉም የፍትሕ አካላት ግዴታ ይሆናል፡፡ በሕገ መንግስቱ ምእራፍ ሶስት የተረጋገጡት መብቶች እና ነጻነቶች ስለሚተረጎሙበት ሁኔታ በተመለከተም በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 13(2) መሠረት ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ሠነዶች መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ መሆን እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ነጻ ሆኖ የመገመት መብት ኢትዮጵያ በተቀበለችው እና የህግ ስርዓቷ አካል ባደረገችው የሲቪልና - ፖለቲካ መብቶች

ቃል ክዳን (ICCPR) አንቀጽ 14 እንዲሁም በሌሎች ስምምነቶች እውቅና የተሰጠው መብት ከመሆኑ አኳያ የዚህ መብት ይዘት ከእነዚህ ስምምነቶች አንጻር ሊመረመር የሚገባው ነው።

የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ተግባራዊነት ለመከታተል የተቋቋመው የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ኮሚቴ ነጻ ሆኖ የመገመት መብት ይዘት በተመለከተ ማብራርያ ሰጥቷል። በማብራርያው መሰረት ነጻ ሆኖ የመገመት መብት የማስረዳት ሸክምን በዓ/ህግ ላይ ሲጥል አጠራጣሪ ነገር ሲያጋጥምም ተከሳሹን በሚጠቅም መልኩ ውሳኔ መሰጠት እንዳለበት ያመለክታል።

ይህ መብት ቀሪ ሊሆን የሚችለው ክስ አቅራቢ የሆነው ዓ/ ህግ ግምቱን ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ በሆነ ሁኔታ የተከሳሽን ጥፋተኝነት በሚያስረዳ ማስረጃ ካፈረሰ ብቻ እንደሆነ ኮሚቴው አብራርቷል። ስለሆነም ነጻ ሆኖ የመገመት መብት በዐቃቤ ሕግ ላይ የሚጥለው የማስረዳት ሸክም ወንጀሉ በተጠርጣሪው ስለመፈጸሙ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ ወጪ የማስረዳት ግዴታ ነው።

ይህን መርህ ስንመለከት በዐቃቤ ሕግ ላይ በህግ የተጣለው የማስረዳት ግዴታ/ሸክም ሁለት ክፍል ያለው ሲሆን እነርሱም ማስረጃ የማቅረብ (burden of production) በቀረበው ማስረጃ ተከሳሽሽ ጥፋተኛ መሆኑን ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ በሆነ ሁኔታ ፍርድ ቤትን የማሳመን (burden of persuasion) ግዴታዎች ናቸው። የቀረበውን የወንጀል ክስ የማስረዳት ግዴታ ዐቃቤ ሕግ እያንዳንዱን የወንጀል አላባውያን ምክንያታዊ ጥርጣሬ በማይፈጥር መልኩ (beyond reasonable doubt) ለፍርድ ቤቱ እንዲያስረዳ ሸክም ይጥልበታል። ዐቃቤ ሕግ ክሱን ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ካላስረዳ በስተቀር ተከሳሽ ንፁህ ነው የሚለው ግምት አይፈርስም። በኮሚቴው በተሰጠው ጠቅላላ አስተያየት መሠረት ነጻ ሆኖ የመገመት መብት ተከሳሽ ከጥርጣሬዎች ተጠቃሚ እንዲሆን ጭምር የሚያደርግ ነው። ይህ ማለት በአንደኛ ደረጃ ወንጀሉ በተከሳሹ ስለመፈጸሙ የሚያጠራጥሩ ነገሮች ሲኖሩ ለተከሳሹ በሚጠቅም አግባብ ሊወሰዱ ይገባል። በሁለተኛ ደረጃ ዐቃቤ ሕግ ያቀረበውን ክስ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በጸዳ አግባብ ካስረዳ በኃላ ተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ በማቅረብ የዐቃቤ ሕግ- ማስረጃን የአስረጂነት አቅም አጠራጣሪ ካደረገው ይህ ጥርጣሬም ተከሳሽን እንዲጠቅም ተደርጎ መወሰድ አንዳለበት ያሳያል። በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 13(2) በምዕራፍ ሶስት ሥር የተዘረዘሩት መብቶችና ነጻነቶች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ሕግጋት ስምምነቶችና መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ መተርጎም የሚገባቸው መሆኑ ተደንግጓል። ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው የሰብአዊ መብት ስምምነቶች ለጉዳዩ ቅርበት ያለው የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንዱ ነው:: ስለዚህ በሕገ መንግስታችን አንቀፅ 20(3) ስር የተደነገገው የተከሳሽ ንፁህ ሆኖ የመገመት መብት እና በአለም አቀፉ የሰቪል እና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀፅ 14(2) ስር ያለው የተከሳሽ ንፁህ ሆኖ የመገመት መብት ይዘት ተመሳሳይነት ያላቸው በመሆኑ ቀሪ ሊሆን የሚገባው በተመሳሳይ መንገድ ነው።

ስለሆነም አሁን በስራ ላይ ያለው የወንጀል ሥነ ሥርዓት ህግ የወጣው እና ወደ ስራ የገባው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት ከመደንጉ እና በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት የሥነ ሥርዓት ሕጉ መተርጎም እና መነበብ ያለበት ከሕገ መንግስቱ ጋር በተጣጣመ አግባብ ነው። በዚህም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት የተረጋገጠው ነጻ ሆኖ የመገመት መብት በዐቃቤ ሕግ ላይ የሚጥለው አነስተኛ የማስረዳት ደረጃ በአንቀጽ 20(3) እና በአለም አቀፉ የሲቪልና የፖለቲካ ስምምነት አንቀጽ 14(2) መሠረት ከምክንያታዊ ጥርጣሬ ውጪ በሆነ ደረጃ የማስረዳት ግደታ ነው።

2. በሕገ መንግስቱ መሠረት የወንጀል ጥፋተኝነት ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በጸዳ ሁኔታ ማስረዳት ምን ማለት ነው?

ከላይ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት እውቅና ያገኘው ነጻ ሆኖ የመገመት መብት በዓቃቢ ሕግ ላይ የሚጥለው አነስተኛ የማስረዳት ደረጃ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በጸዳ ሁኔታ የማስረዳት ግዴታ እንደሆነ በጉባኤው ድምዳሜ ላይ ተደርሷል፡፡ ነገር ግን ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በጸዳ ሁኔታ ማስረዳት ምን ማለት ነው የሚለው ጭብጥ መልስ ማግኘት አለበት፡፡ ከማስረዳት ደረጃ ጋር ተያይዞ ለተለያዩ አላማዎች ተፈጻሚነት ያላቸው የተለያዩ የማስረጃ ደረጃዎች በስራ ላይ ይገኛሉ፡፡ በማስረጃ ህግ ጽንሰ ሃሳብ እና የዳበረ ልምድ ካላቸው ሌሎች አገሮች ልመድ መረዳት እንደሚቻለው ከእነዚህ የማስረዳት ደረጃዎች መካከል reasonable suspicion (በቂ ጥርጣሬ) probable couse (ምክንያታዊ ጥርጣሬ) preponderance of evidence (ሚዛን የሚደፋ ማስረጃ) clear and conving evidence (ግልጽ አእና አሳማኝ ማስረጃ) beyond reasonable doubt (ከምክንያታዊ ጥርጣሬ የጸዳ ማስረጃ) ለመጥቀስ እንችላለን፡፡ እዚህ የተጠቀሱት የማስረዳት ደረጃዎች ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ በቅደም ተከተል የተቀመጡ ሲሆን ተፈጻሚነታቸውም ለተለያዩ ክርክሮችን የሚመክት ነው፡፡

በቂ ጥርጣሬ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ በብዛት ተፈጻሚነት የሚኖረው አንድ ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ የተጠረጠረ ሰው በማስቆም ለመበርበር ወይም የቤት ለቤት ፍተሻ ለማድረግ ዝቅተኛው መመዘኛ ነው፡፡ በወ/ሥ/ሥ/ሕጉም በአንቀጽ 32 መሠረት ፖሊሰ አንድ ሰው በተከሰሰበት ወንጀል ወይም ወንጀል ሠርታል ተብሎ በተጠረጠረበት ነገር ማስረጃ የሚሆን በሰውነቱ ደብቋል የሚያሰኝ በቂ ጥርጣሬ ካለው ለመበርበር እንደሚችል ደንግጓል፡፡ በዚህ የመመዘኛ ደረጃ ውሳኔ ለመድረስ በሰዎች ነጻነት ላይ ዝቅተኛ መጋፋት የሚያደርሱ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ከመበርበር በዘለለ አንድን ሰው በመያዝ ለጊዜው በማቆያ ስፋራ ለማቀየት ወይም በእስር ቁጥጥር ስር ለማድረግ የፖሊስ ባልደረባው አርምጃው ለመውሰድ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ያለው መሆኑ ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡

በፍትሐብሔር ክርክሮች በተመለከተ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ የሚሰጠው ሚዛን በሚደፋ ደረጃ የማስረዳት ግዴታውን ለተወጣ ተከራካሪ ወገን ነው፡፡ ይህም የማስረዳት ሸክም ያለው ወገን ክርክሩን በተሻለ ሁኔታ የማስረዳት ግዴታ ያለው መሆኑ ያሳያል፡፡ በዚህም ዳኛው በሚያደርገው የማስረጃ ምዘና ከተከራካሪ ወገኖች መካከል በተሻለ ወይም ሚዛን በሚደፋ አግባብ ክርክሩን ያስረዳ ወገን የፍርድ ባለመብት የሚያደርግበት አግባብ ነው፡፡

በፍትሐብሔር ክርክር ተፈጻሚነት ያለው ሌላው የማስረዳት ደረጃ ግልጽ አና አሳማኝ ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ የሚጠይቀው የማስረዳቱ ደረጃ ነው፡፡ ግልጽና አሳማኝ በሆነ ደረጃ ማስረዳት በዋናነት በፍ ትሐ ብሔር ጉዳዮች የህጻናት ሞግዚትነት መብት ለማሳጣት የሚቀርቡ ክርክሮች እና ሌሎች መሰል ከባድ እንደምታ ያላቸው ውሳኔዎች ለመስጠት ወይም በወንጀል ጉዳይ የቅድመ ምርመራ እስር ለመፍቀድ በተግባር ላይ የሚውል መመዘኛ ነው፡፡ አነዚህ ከባድ ውሳኔዎች ለመወሰን ዳኛው ግልጽ እና በማያሻማ ሁኔታ ውሳኔውን ለመስጠት የሚያስችሉ ማስረጃዎች አንዲቀርቡለት ይጠበቃል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት መመዘኛዎች የላቀው እና ወደ እርግጠኝነት የተጠጋው የማስረዳት ግዴታ የሚጥለው መመዘኛ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በጸዳ አግባብ የማስረዳት ደረጃ ነው፡፡ ይህ የማስዳት ደረጃ ከላይ ከጠቀስናቸው የማስረጃ ደረጃዎች አንጻር በዐቃቢ ሕግ ወንጀሉ በተከሳሹ ስለመፈጸሙ በማያጠራጥር ሁኔታ ሊያስምን የሚችል ማስረጃ እንዲያቀርብ የሚያስገድድ ነው፡፡ ዐቃቢ ሕጉ

ያቀረባቸው ማስረጃዎች ተከሳሹ ወንጀሉ ስለመፈጸሙ አንድን ምክንያታዊ የሆነ ሰው ጥርጣሬ ውስጥ የሚከቱ ከሆነ ተከሳሹ ጥፋተኛ መባል አይኖርበትም።

ወንጀሉ በተከሳሹ ስለመፈጸሙን መቶ ፐርሰንት በሚያረጋግጥ ማስረጃ ማስረዳት የማይጠበቅበት ቢሆንም ዐቃቢ ሕግ የሚያቀርበው ማስረጃ ግን ወደ እርግጠኝነት በተጠጋ ሁኔታ ተከሳሹ ወንጀሉን መፈጸሙን የሚያረጋግጡ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

በዚህም ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ወንጀሉን ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በጸዳ ወይም ወደ እርግጠኝነት በተጠጋ ሁኔታ ካላስረዳ ተከሳሹ ጥፋተኛ መባል የለበትም። ስለሆነም በወንጀል ጉዳይ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ለመስጠት ፍርድ ቤቱን ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በጸዳ ሁኔታ (ለእርግጠኝነት በተጠጋ ሁኔታ) የሚያሳምን ጠንካራ ማስረጃ ካልቀረበለት በቀር ዐቃቢ ሕጉ በቂ ማስረጃ ማቅረቡ ብቻ ተከሳሹን ጥፋተኛ ማድረግ አይገባም።

የዳበረ የሕግ ልምድ ካላቸው አገሮች ልምድ መረዳት እንደሚቻለው በወንጀል የተከሰሰ ሰው ጥፋተኛ ለማሰኘት ዐቃቢ ሕግ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ ውጪ እንዲያስረዳ የሚጠበቅበት ዋና ምክንያት የወንጀል ጥፋተኝነት እና ቅጣት የሰዎችን ተፈጥሮአዊ ነጻነት ከማሳጣቱ በተጨማሪ ሰዎች በማህበረሰቡ ዉስጥ ያላቸው ተቀባይነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚፈጥር ነው። በዚህም በወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎች ጥፋተኛ ሊባሉ እና ሊቀጡ የሚገባቸው የተጠረጠሩበትን ወንጀል ስለመፈጸማቸው በማያሻማ ሁኔታ በማስረጃ ሲረጋገጥ ነው። በዚህም ነጻ ሆኖ የመገመት መብት ሰዎች በተሳሳተ መንገድ በወንጀል ጥፋተኛ እንዳይባሉ፣ ነጻነታቸውን አለአግባብ እንዳያጡ፣ እውነተኛ ጥፋተኞች በመለየት ሕብረተሰቡ ከወንጀል ለመከላከል እና በፍርድ ቤቶች የሚሰጡት ውሳኔ ቅቡልነት ለማስጠበቅ አይነተኛ መሳሪያ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል።

3. ፍርድ ቤቱ በአመልካች ላይ የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በሕገ መንግስቱ ከተረጋገጠው ነጻ ሆኖ ከመገመት መብት ጋር የሚቃረን መሆን አለመሆኑ?

አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ የቅጣት ውሳኔ የተላለፈበት የጦር መሳሪያ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 4(2) ን በመተላለፍ ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ በንግድ ቤት ውስጥ ደብቀዋል በሚል ክስ ነው። የአዋጁን አንቀጽ 4(2) ስንመልከት የፀና ፍቃድ ሳይኖረው የጦር መሳሪያ መያዝ፤ ማስቀመጥ ወንጀል ያደርጋል። ከዚህ አንቀጽ መረዳት አንደሚቻለው ዐቃቤ ሕግ ያለበት ግዴታ ፈቃድ ሳይኖረው መሳሪያውን ተከሳሹ ማስቀመጡን ማስረዳት ነው።

ህገወጡ የጦር መሳሪያ የተገኘው በአመልካች የንግድ ቤት ሲሆን ለፖሊስ ጥቆማ ያቀረበችው ደግሞ ባለቤቱ ናት። ለዚህም ዐቃቢ ሕግ መሳሪያውን ያገኙትን ፖሊሶች ምስክርነት አሰምቷል። አመልካች በበኩሉ ፍርድ ቤት ቀርቦ ወንጀሉን አለመፈጸሙን ከመናገሩ በተጨማሪ ከባለቤቱ ጋር ጸብ ላይ የነበረ መሆኑ እና የፍቺ ሂደት ላይ መሆናቸውን ክሱንም በዚህ መነሻ ያቀረበች መሆኑን፤ ህገ-ወጥ የጦር መሳሪያው የተገኘበት ንግድ ቤት እርሱ እንደማይሄድና ባለቤቱ እንደምትሰራበት፤ መሳሪያዎቹ የተገኙበት ካዝና ውስጥም ማታ ማታ ባለቤቱ የሚሸጡ ሞባይሎች እንደምታሳድርና ቁልፉም በእርሷ እጅ እንደሚገኝ የሚያስረዱ ምስክሮችን አቅርቧል።

በዐቃቢ ሕግ የቀረቡት ምስክሮች የጦር መሳሪያው በአመልካች ንግድ ቤት መገኘቱ የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡ ቢሆንም የጦር መሳሪያው አመልካች በንግድ ቤቱ ያስቀመጠ ስለመሆኑ ቃላቸውን አልሰጡም። ስለሆነም የንግድ ቤቱ የአመልካች ባለቤት የሚሰሩበት እና አመልካች በንግድ ቤቱ የማይገኙ ስለመሆኑ አመልካች ባቀረባቸው ምስክሮች በተረጋገጠበት ሁኔታ የጦር መሳሪያው በአመልካች የንግድ ቤት ሊገኝ የቻለው አመልካች የጦር መሳሪያው በማስቀመጣቸው ሊሆን

አይችልም፡፡ አመልካች በንግድ ቤቱ የማይገኙ እና በንግድ ቤቱ የሚገለገሉት የአመልካች ባለቤት መሆናቸው ከተረጋገጠ በምን አግባብ አመልካች ይህንን የጦር መሳሪያ በዚህ የንግድ ቤት ሊያስቀምጡ እንደቻሉ ዐቃቢ ሕግ የማስረዳት ግዴታ አለው፡፡ ይህ ሳይሆን ሲቀር ግን አመልካች በንግድ ቤቱ ሳይገኙ የጦር መሳሪያው በንግድ ቤቱ የተገኘው አመልካች ስለአስቀመጡት ነው ለማለት የሚቻል አይሆንም፡፡

በሕገ መንግስታችን አንቀፅ 20(3) ስር እውቅናና ጥበቃ የተሰጠው ንፁህ ሆኖ የመገመት መብት በዐቃቤ ሕግ ላይ የሚጥለው አነስተኛው የማስረዳት ሸክም መመዘኛ "ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በጸዳ ሁኔታ" የማስረዳት ግዴታ እንደሆነ ጉባኤው ከላይ መደምደምያ ላይ ደርሷል፡፡ ዐቃቢ ሕግ ይህን መመዘኛ የሚያሟላ ማስረጃ ያቀረበ ከሆነ ተከሳሽ ንጹህ ሆኖ የመገመት መብቱ በጊዜያዊነት ቀሪ እንዲሆን በማድረግ የማስረዳት ሸክምን ወደ ተከሳሽ ያሸጋግራል፡፡፡ ተከሳሽ ደግሞ ይህን መብት ወደ ነበረበት ሁኔታ ለመመለስ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የማስረዳት አቅም ላይ "ምክንያታዊ ጥርጣሬ" መፍጠር ይሆናል፡፡

በሌላ አገላለጽ በየትኛውም ደረጃ ተከሳሽ ንፁህ መሆኑን ማስረዳት አይጠበቅበትም፤ እንዲህ ዓይነት መመዘኛ ሕገመንግስታዊ አይሆንም፡፡ ተከሳሽ ማድረግ የሚጠበቅበት ተከሳሽ ወንጀል እንደፈፀመ ለማስረዳት ዐቃቤ ሕግ ያቀረበው ማስረጃ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ ያልፀዳ መሆንና በዚህ ማስረጃ የማስረዳት አቅም መተማመን እንደማይገባ ማሳየት ብቻ ነው፡፡

ከጅምሩ ዐቃቤ ሕግ መሳሪያው በአመልካች ንግድ ቤት በፍተሻ መገኘቱን ከማሳየት በዘለለ መሳሪያውን ከአመልካች ጋር በቀጥታ ምን እንደሚያገናኘው ያላስረዳ በመሆኑ ክሱን ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በጸዳ ሁኔታ (beyond reasonable doubt) አረጋግጧል ለማለት አይቻልም፡፡ በመቀጠል አመልካች ካቀረባቸው ምስክሮች ቃል አንጻር በተለይም ጥቆማው በሚስቱ የቀረበ መሆኑ፣ ከሚስቱ ጋር ጸብ ላይ መሆናቸውና በፍቺ ሂደት ላይ ያሉ መሆናቸው፤ ህገ-ወጥ የጦር መሳሪያው የተገኘበት ንግድ፤ ቤት እርሱ እንደማይሄድና ባለቤቱ እንደምትሰራበት ማስረጃ መቅረቡ፤ መሳሪያው የተገኘበት ካዝና ውስጥ ማታ ማታ ባለቤቱ የሚሸጡ ሞባይሎች አንደምታሳድርና ቁልፉም በእርሷ እጅ አንደሚገኝ ምስክሮቹ ማስረዳታቸው ሲታይ በአንድ ምክንያታዊ ሰው ላይ የተከሳሽን ጥፋተኝነት አስመልክቶ በቂ ጥርጣሬ የሚፈጥር ነው፡፡፡

የአመልካች የመከላከያ ማስረጃ መሳሪያው የእርሱ ላይሆን እንደሚችል ወይም እርሱ ያስቀመጠው ስላለመሆኑ ምክንያታዊ የሆነ ጥርጣሬ የሚፈጥር ነው፡፡ የተከሳሽ መከላከያ ማስረጃ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ ያልፀዳ መሆኑን እና በዚህ ማስረጃ የማስረዳት አቅም መተማመን አንዳማይገባ ማሳየት ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ፍርድ ቤቶች በአመልካች ላይ የሰጡት የጥፋተኝነት ዉሳኔ የአመልካችን ንጹህ ሆኖ የመገመት ሕገ መንግስታዊ መብት የሚጥስ ነው፡፡

በመሆኑም ከላይ በሰጠነው 1 እና 2 የሰጠናቸው ዝርዝር የሕገ መንግስት ትርጉም ትንታኔን መሠረት በማድረግ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሕገ መንግስታዊነትን በተመለከተ የሚከተሉት ድምዳሜዎች ላይ በጉባኤው ተደርሷል፡-

- በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 20(3) መሠረት ነጻ ሆኖ የመገመት መብት በዐቃቤ ህግ ላይ የሚጥለው አነስተኛ የማስረዳት ደረጃ ወንጀሉ በተከሳሽ ስለመፈጸሙ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በጸዳ ሁኔታ የማስረዳት ሸክም ነው፡፡
- ፍርድ ቤቱ በዓቃቢ ሕግ የቀረበው ማስረጃ አመልካች ካቀረበው ማስረጃ አንጻር በተሻለ ሁኔታ ወንጀሉ ስለመፈጸሙ ያሳምናል በማለት በአመልካች ላይ የጥፋተኝነት እና የቅጣት

ውሳኔ ማስተላለፉ፣ አመልካች በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 20(3) ከተረጋገጠለት ነጻ ሆኖ የመገመት መብትን የሚቃረን ነው፡፡

በመሆኑም፡-

1. በኦሮሚያ ክልል የምሥራቅ ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 64850 በቀን 25/04/2014 ዓ.ም በአመልካች ላይ የሰጠው ውሳኔ እና በመጨረሻም በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 221848 በቀን 04/08/2014 ዓ.ም የጸናው ውሳኔ ከሕገ መቀማስቱ አንቀጽ 20(3) ጋር የሚቃረን በመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም እንዲባል፤
2. አመልካች በተከሰሰበት ወንጀል ላይ ዐቃቤ ሕግ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ በሆነ ማስረጃ ያላስረዳ በመሆኑ በአመልካች ላይ የተጣለው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተፈጻሚ ሊሆን አይገባም ሲል ጉባኤው ይህንን የውሳኔ ሃሳብ በሙሉ ድምጽ ለመጨረሻ ውሳኔ ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት አቅርቧል፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት ያለው ስለሆነ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሙሉ ድምጽ አጽድቋል፡፡

ትዕዛዝ

1. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ያቀረቡት የውሳኔ ሀሳብ በምክር ቤቱ ሙሉ ድምጽ ጸድቋል፡፡
2. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በምክር ቤቱ ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም የውሳኔ ግልባጭ ይድረሰው፡፡
3. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ በሙሉ ድምጽ የጸደቀ ስለሆነ እንዲያውቀው የውሳኔ ግልባጭ ይድረሰው፡፡
4. አመልካች የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ በምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ የጸደቀ ስለሆነ እንዲያውቁት የውሳኔ ግልባጭ ይድረሳቸው፡፡